# የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት መመሪያን ለማሻሻል በተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ላይ የቀረበ አጭር ማብራሪያ

ረጅም የግብይት የእሴት ሰንሰለት ለምርት ብክነትና የጥራት መጓደል፤ ህገ ወጥ ግብይት፣ የኮንትሮባንድ መስፋፋት እና ምርትን በክምችት መደበቅ ለመሳሰሉት ችግሮች የሚዳርግ በመሆኑ እና ይህም በውጭ ንግድ አፈጻጸማችን ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ በቅባት እህሎች እና በጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እንደ አንድ መፍትሄ ተወስዶ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት መመሪያ ቁጥር 1026/2017 ወጥቶ ተግባራዊ መደረጉ ይታወቃል፡፡

ሆኖም በመመሪያው አንቀጽ 4 ላይ የተካተተው በሰነድ አረጋጋጭ አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ ውል የማቅረብ ግዴታ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሌሎች ግዴታዎች ላኪዎችን እና አቅራቢዎችን ለተጨማሪ ወጪ እና ለተራዘመ የግብይት አፈጻጸም የዳረጋቸው መሆኑን ከወዲሁ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ወቅቱ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች ለሀገር ውስጥ እና ለውጪ ገበያ የሚቀርቡበት ወሳኝ ጊዜ በመሆኑ አፋጣኝ ማሻሻያ ካልተደረገ በውጭ ንግድ አፈጻጸማችን እና የውጭ ምንዛሪ ግኝታችን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ከውል ጋር የተያያዙ የመመሪያውን ድንጋጌዎች ማሻሻል የቀጥታ ግብብይት ትስስሩን እና የውጭ ንግድ አፈጻጸማችንን የተሳለጠ እንደሚያደርገው ስለታመነበት ይህ የማሻሻያ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

መመሪያው በአጠቃላይ 4 አንቀጾችን የያዘ ሲሆን በአንቀጽ 1 አጭር ርዕሱን፣ በአንቀጽ 2 ማሻሻያዎችን፣ በአንቀጽ 3 የመሸጋገሪያድንጋጌን እና በመጨረሻም በአንቀጽ 4 የሚጸናበትን ጊዜ እንዲያካትት ተደርጓል፡፡

የማሻሻያ አንቀጽ 2 በሥራ ላይ ባለው መመሪያ ቁጥር 1026/2017 ላይ ሥልጣን ባለው አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ ውል የማቅረብ ግዴታ የሚጥሉትን አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) እና 4 (3) እንዲሁም ከዚህ ግዴታ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት አላቸው ተብሎ የታመነባቸውን አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) እና 15 (2) በመሰረዝ በአዲስ ድንጋጌ የሚተካ ሲሆን ቀደም ሲል የተደረጉ ውሎችን ተፈጻሚነት በተመለከተም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት እንደሚወሰን የሚገልጽ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ አካትቷል፡፡

ስለሆነም የፍትህ ሚኒስቴር የመመሪያውን አስፈላጊነት ተገንዝቦ እንዲመዘግብልን በአክብሮት አቅርበናል፡፡



የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration
Archives
መዝገብ ቤት

CamScanner

# <u>መመሪያ ቁጥር 1033/2017</u>

## <u>የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) መመሪያ</u>

የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይትን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1026/2017 ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 (4) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ **"የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት መመሪያ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 1033/2017"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2..<u>ማሻሻያ</u>

የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይትን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1026/2017 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፡፡

"1/ማንኛውም አቅራቢ እና ላኪ በዚህ መመሪያ መሰረት በሚፈጠር የግብይት ትስስር የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ማካሄድ ይችላል፡፡"

2. የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዟል፡፡

3. የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፡፡

"2/ የቀጥታ ግብይት ትስስር ለገባለት ላኪ ማስረከብ ያለበትን ምርት አቅርቦ ሳያጠናቅቅ ለሌላ ገዥ ሽያጭ ያለመፈጸም፤"



የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት

CamScanner

4. የመመሪያው አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፡፡

"2/ የቀጥታ ግብይት ትስስር ለገባለት ላኪ ማስረከብ ያለበትን ምርት አቅርቦ ሳያጠናቅቅ ለሌላ ገዥ ሽያጭ መፈጸም፤"

3. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተደረገ ውል የተፈጻሚነት ሁኔታ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሆኖም ተዋዋይ ወገኖች ካልተስማሙ መብትና ግዴታቸዉ በዉሉ መሰረት ይሆናል፡፡

4. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በሚንስቴሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ 8 ቀን 2017 ዓ.ም

ካሳሁን ጎፌ ባለሚ (ፒ.ኤች.ዲ)

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት



CamScanner